# ለመሆኑ፤ ይኼ ትግል የማንነው?

አንዱዓለም ተፈራ - የእስከመቼ አዘጋጅ

ቅዳሜ፤ ግንቦት ፲፭ ቀን፤ ፳ ፻ ፯ ዓመተ ምህረት ( 5/23/2015 )

እስኪ በመጀመሪያ አንባቢየን ልጠይቅ! ለመሆኑ ይኼ ትግል የማነው? ጥያቄው መሠረታዊ ነው። ለዚህ የምንሠጠው መልስ፤ ከዚያ በኋላ መከተል ላለባቸው ጉዳዮች በሙሉ ወሳኝ ነው። ያለጥርጥር ይህ ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ነው። ትግሉ ደግሞ በኢትዮጵያ ሕዝብና በሥልጣን ላይ ተቀምጦ፤ ሕዝቡን በማሰቃየትና ሀገሪቱን ወደ አዘቅት በመከተት ላይ ባለው የትግሬዎች ነፃ አውጪ ግንባር ቡድን መካከል ነው። በድርጅቶች መካከል ያለ ምርጫ አይደለም። በሕዝቡ ተወክሉም ወይም ራሳቸውን ወክሉ፤ በውጭ ሀገር፤ በፖለቲካ ትግሉ ምኅዳር የተሰለፉ የትግል ድርጅቶች አሉ። እንግዲህ እዚህ ላይ፤ ኢትዮጵያዊ የሆኑትን ማለቴ ነው። በተጨማሪም፤ የዚህ ጽሑፍ መልዕክት፤ በውጪ ሀገር ያሉ ታጋይ ድርጅቶችን ብቻ ነው የሚመለከተው።

ታዲያ ትብብር ሲባል፤ በነዚህ ድርጅቶች እና ታታሪ ታጋይ ግለሰቦች መካከል ነው። ተደራጅተው በመገኘታቸው፤ ታጋይ ድርጅቶች ከፍ ያለ ሚና አላቸው። ትብብርን በሚመለከት፤ ሕዝቡ በአንድነት፤ **"ተባበሩ ወይንም ተሰባበሩ!"** እስኪል ድረስ ጩኸቱን አሰምቷል። በዚህ ሳምንት፤ ባልኅበኘኋቸው የኢትዮጵያዊያን ድረገጾች ስሸከረከር፤ የአቶ ዮሴፍ መርሻንና የአቶ እያሱ ዓለማየሁን ጽሑፎች አነበብኩ። በቪዲዮ ደግሞ የዶክተር ብርሃኑ ነጋን ንግግር አዳመጥኩ። ገረመኝ። እስከዛሬ ተባበሩልን የሚባሉት ጉምቱዎቹ እነህ አልነበሩም እንዴ? ጠሪዎቹ ሆነው ሳገኛቸው፤ ደስ አለኝ።

የአቶ መርሻ ዮሴፍ ጽሑፍ ርዕስ እንዲህ ይላል፤ **"በአንድነት ስንቆም ኃያል ነንና ዛሬም እንደወትሯችን እናብር!!"**

በተመሳሳይ መልኩ፤ አቶ እያሱ ዓለማየሁ መተባበር የግድ አለብን የሚሉ መልዕክቶችን አስፍረዋል።

ዶክተር ብርሃኑ ነጋም በቪዲዮው፤ መተማመን፣ ትብብርና አብሮ መሥራት የግድ እንዳለብን አስምረዋል።

በግለሰብ ደረጃና በየተሰባሰቡበት ሁሉ፤ አቶ አባንግ ሜቶ፣ ኮሎኔል ሮቤል አባቢያ፣ ዶክተር አበባ ፈቃደ፣ ዶክተር መሳይ ከበደ፣ ዶክተር አክሎግ ቢራራ፣ ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገብረማርያም፣ አቶ አክሊሉ ወንድአፈረው፣ አቶ አበበ በለው፤ በጽሑፍም በንግግርም ይኼኑ ሲሉ ተደምጠዋል። የግለሰቦቹን ለጊዜው ላቆየውና፤ ሸንጎና የሽግግር መንግሥት ካዉንስል በተደጋጋሚ ይኼኑ ዋና መልዕክታቸው አድርገው፤ ይሯሯጣሉ። ታዲያ ምኑ ላይ ነው ጉድለቱ። ይኼ ትግል የማነው? ጠሪው ማነው? ተጠሪው ማነው። የትኛው ድርጅት ነው ኑ ሳይባል ቀርቶ፤ ኑ እያለ ጥሪ ያላቀረበ?

እስኪ ወደ መጀመሪያዎቹ ሶስቱ ጉምቱ መሪዎች ልመለስ። አቶ መርሻ ዮሴፍ! እርስዎ ጥሪ አቅርበዋል። አቶ እያሱ ዓለማየሁ እርስዎ ጥሪ አቅርበዋል። ዶክተር ብርሃኑ ነጋ! እርስዎ ጥሪ አቅርበዋል። ይህ ትግል የናንተ ነው። የናንተ ያልኩበት ምክንያት፤ ሕዝቡን ወክላችሁ ሕዝባዊ ትግል እያካሄዳችሁ ስለሆነ ነው። ታዲያ ተጋባዥ ማነው? ጋባዥስ ማነው? ጋብዛችኋል። ተጋብዛችኋል። መቸም አልኩ ለማለት ጥሪውን አቀረባችሁ የሚል ወንጀል ፈጽሞ አይወጣኝም። ታዲያ ምንድን ነው የምትጠብቁት?

እንዲህ ይሁን። ለመሰባሰብ ፈቃደኛ ብቻ ሳትሆኑ፤ ሰብሳቢም ለመሆን ጥሪ አቅርባችኋል። በጄ! አንዳችሁ ለሌላችሁ መልስ መሥጠት አልወደዳችሁም። ፍቀዱልኝና እኔ ነኝ አልወደዳችሁም ያልኩ። ጥፋቱ ከኔ ይሁን። እናም ልክስ ዝግጁ ነኝ። አንዳችሁም ንጹህና ጉድለት የሌለው አይደላችሁም። እኔም ብዙ ጉድለት አለኝ። ተሰባስበን እንከላዋለን። እርስበርስ ተጠራርታችሁ ስላልተገናኛችሁ፤ እኔ አገናኝ ልሁን። አስፈላጊውን ወጪም እራሳችሁ የማትችሉ ከሆነ፤ ሲሆን ረዳቶችን በማግኘት፤ አለያም ከዚህ የበለጠ ያገሬ ጉዳይ የለምና፤ እኔው ወጪውን ችዬ ላገናኛችሁ። ምንም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ የለበትም። በቀጥታና በግልጽ መልስ ሥጡኝ። ባንድነት የት እንደምንገናኝና መቼ እንደምንገናኝ፤ መልሱን ስትሠጡኝ እንወስናለን። የትግሉ ባለቤቶች፤ ሲሆን ጋባዥ አያስፈልጋቸውም። ከሆነም በኔ ይሁንና ልጋብዛችሁ። እኔን ለመርዳት የምትሹ ግለሰብ ታታሪዎች ሁሉ፤ ጉዳዩ የናንተም ስለሆነ፤ እባካችሁ ወደኋላ አትበሉ፤ እርዱኝ! መወታቀቫና መወዳደሻ ሰዓቱ አልቋል። የተግባር ሰዓቱ ተደውሏል። ሀገር ከሁሉም ይበልጣል። በሀገር የጎደለብንን እንስተካከላለን።

የትግል ባለቤትነትን የጠየቅሁት ወድጄ አይደለም። ከኔ የከበዱ፤ ከኔ የበለጠ የትግል ልምድና የትምህርት ልቀት ያላቸው ሊያገናኟችሁ ሞክረዋል። እኔ በልጩ አይደለም። ራሳችሁ የጠራችሁትን፤ ትግላችሁ የኔ ትግል በመሆኑ፤ ደፍሬ እጄን ዘረጋሁ። እናንተው ያላችኋቸውን መልሼ ለናንተው ብተርክ ስድብ ነው። አስፈላጊነቱ፣ ወቅታዊነቱ፣ . . . አጉል ድፍረት ይሆንብኛል። እናም ባደባባይ የናንተውን ጥሪ ለናንተው አድርጌያለሁና፣ መልስ ሥጡኝ። አንባቢም በትኩረት ይከታተለው። አቶ ዮሴፍና አቶ እያሱ የግል ቁጥሬ ስላላችሁ፤ ባመቻችሁ ጊዜ ልትደውሉልኝ ትችላላችሁ። ዶክተር ብርሃኑም ቁጥሬን ማግኘት አይርቅዎትም። አስፈላጊ ከሆነም በኢሜል ለያዳንዳችሁ እልካለሁና ከዚህ ሥር ባለው የኔ ኢሜል መልስ ሥጡኝና ስልኬን እልክላችኋለሁ። ባሁኑ ሰዓት ዋናው የታጋይነት መለኪያው፤ ለትብብር የምናሳየው ፈቃደኝነት ነው። እስኪ ምሩን። ፈቃደኛ በመሆንም እኮ ይመራል። እኔ ደግሞ

ሀገሬ ላለችበት ሁኔታ ማድረግ የምችለውን ሁሉ ለማድረግ ወደኋላ አልልም።

ይህ ትግል የሚቀጥለው ትውልድ ትግል አይደለም። ይህ ትግል ያለፈው ትውልድ ትግል አይደለም። ይህ ትግል የኛ ነው። ባላቤትነቱና ኃላፊነቱን በድፍረት እንውሰድ። እንቆጠር። ዛሬ ነው ትግሉ። ዛሬ ነው ኃላፊነታችን። ዛሬ ከታጋዩ ሕዝባችን ጎን እንሰለፍ። ሕዝቡ እየታገለ ነው።

ከታላቅ አክብሮት ጋር

ምንጊዜም ኢትዮጵያዊ

አንዱዓለም ተፈራ **eske.meche@yahoo.com**

**Directly emailed to:**

አቶ መርሻ ዮሴፍ **ms38498@yahoo.com**

አቶ እያሱ ዓለማየሁ **iyasou19@aol.com**

ዶክተር ብርሃኑ ነጋ **org@ginbot7.org followup@ginbot7.org**

**Copies sent to:**

ኢትዮሽንን የሽግግር መንግሥት ካውንስል

አቶ ኦባንግ ሜቶ፣ ኮሎኔል ሮቤል አባቢያ፣ ዶክተር አበባ ፈቃደ፣ ዶክተር አክሎግ ቢራራ፣ ዶክተር መሳይ ከበደ፣ ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገብረማርያም፣ አቶ አክሊሉ ወንድአፈረው፣ አቶ አበበ በለው፤

አቶ አብረሃ በላይ፣ አቶ ግርማ በቀለ፣ ዶክተር እምሩ አሰፋ

ከዚህ በተረፈ፤ በድረገጻቸው ያወጡት ዘንድ፤ ለኢትዮጵያዊ ድረገጽ አርታዒዎች እልከዋለሁ።